# የሕብረት ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር የተሻሻለ

# የመመስረቻ ጽሑፍ (ረቂቅ)

መስከረም 2017 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

ማውጫ


የዚህ ሠነድ ዓላማ ..........................................................................4

ምዕራፍ አንድ..........................................................................................4

የአክሲዮን ማሕበሩ አደረጃጀት፣ ዓላማዎች እና ባለአክሲዮኖች.......................... 4

የአክሲዮን ማህበሩ ስም ........................................................................ 4

የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ፣ ቅርንጫፎች እና ተቀጥላ ማህበራት .......4

የአክሲዮን ማህበሩ የንግድ ዓላማዎችና የሥራ መስክ......................................4

ምዕራፍ ሁለት........................................................................................ 6

የአክሲዮን ካፒታል፣ ከአክሲዮን የሚመነጩ የባለአክሲዮኖች መብቶችና ግዴታዎች..6

የአክሲዮን ማህበሩ ዋና ገንዘብ /ካፒታል/ ................................................6

የአክሲዮን ይዞታ ገደብ ........................................................................ 6

የአክሲዮኖች ዓይነትና መደብ ............................................................... 6

የባለአክሲዮኖች ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፤ የፈረሙትን የአክሲዮን ብዛትና የተከፈለውን የገንዘብ መጠን ........................................................................ 7

የአክሲዮኖች አከፋፈልና ቀሪ ዋጋቸው ላልተከፈለ አክሲዮኖች ስለሚኖር ኃላፊነት....7

ከአክሲዮን ይዞታ የሚመነጩ የባለአክሲዮኖች መብቶችና ግዴታዎች ............... 7

የአክሲዮን የጋራ ባለቤቶች መብትና ኃላፊነት ............................................8

በመያዣ ወይም በአላባ ስለሚሰጡ አክሲዮኖች ...........................................9

የባለአክሲዮኖች መዝገብ ...................................................................... 9

አክሲዮኖች ለሌላ ወገን ስለማስተላለፍ .................................................. 9

ምዕራፍ ሦስት ......................................................................................... 10

የአክሲዮን ማህበሩ የሥራ አመራር አካላት እና ሥልጣን ............................ 10

የአክሲዮን ማህበሩ የሥራ አመራር አካላት ........................................... 10

የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ............................................................. 10

የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር ..................................... 11

የጠቅላላ ጉባዔዎች የጥሪ ማስታወቂያ እና በባለአክሲዮን መዝገብ ስለመጻፍ ...... 13

ውክልና ..................................................................................... 13

የጥቅም ግጭት ............................................................................ 14

መደበኛና አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች ለማካሄድ ስለሚያስፈልገው ምልዓተ-ጉባዔ

እና ውሳኔ የሚተላለፍበት ድምጽ ........................................................... 14
የጠቅላላ ጉባዔ ቃለጉባዔዎች ........................................................... 15
የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን መሰየም እና የሥራ ዘመን ......................... 16
የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር ................................................ 17
ለማህበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ ........................................... 17
የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣንና ተግባር .............................................. 17
የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ የስብሰባ ቦታ፣ አጠራር እና
የአሰራር ደንብ........................................................................... 19
የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ........................................................... 20
ዳይሬክተሮችን ስለመተካት ............................................................. 20
አክሲዮኖችን በዋስትና ስለማስቀመጥ .................................................. 21
የዋና ስራ አስፈፃሚ እና ምክትል ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎች ..................... 21
የዋና ሥራ አስፈፃሚ ሥልጣንና ተግባር ............................................... 22
የውጭ ኦዲተሮች ስያሜ፤ ኃላፊነትና ተግባር ......................................... 24
የማህበሩ ጸሐፊ ሹመት፤ ሥልጣንና ተግባር .......................................... 24
ምዕራፍ አራት ................................................................................. 25
ስለአክሲዮን ማሕበሩ ሂሳብ አያያዝና ተዛማጅ ተግባራት............................ 25
ጠቅላላ ድንጋጌዎች ...................................................................... 25
የፋይናንስ መዝገቦችና መረጃዎች ...................................................... 25
የማህበሩ የሂሳብ ዓመትና ሪፖርት ..................................................... 26
የሂሳብ ሠነዶችን እና ሪፖርቶችን ስለመስጠት........................................ 26
በጥሬ ገንዘብ ስለሚያዙ ሂሳቦችና የመጠባበቂያ ገንዘብ ............................ 26
በችልተኝነት ወይም እምነት ማጉደል ምክንያት ለሚደርሱ ኪሣራዎች
የሚሸፈኑባቸው መጠባበቂያዎች......................................................... 27
ሌሎች የመጠባበቂየ ሂሳቦች .......................................................... 27
የትርፍ ድርሻ አመዳደብና አከፋፈል.................................................... 28
ካፒታል በሚቀነስበት ጊዜ የሚደረግ የትርፍ ክፍፍል ዕገዳ ........................ 28
ስለምዝገባና ሪፖርቶችን ይፋ ስለማድረግ ............................................ 28
ምዕራፍ አምስት ...............................................................................29

ስለአክሲዮን ማሕበሩ መፍረስ እና ሂሳብ ስለማጣራት ................................ 29

የአክሲዮን ማህበሩን ለማፍረስ የሚያበቁ ምክንያቶች እና አግባብነት ያላቸው ሥነ-ሥርዓቶች ........................................................................... 29

ምዕራፍ ስድስት ........................................................................... 30

ሌሎች ድንጋጌዎች ........................................................................... 30

አክሲዮን ማህበሩ በሥራ የሚቆይበት ጊዜ .................................................. 30

ልዩ ልዩ ጉዳዮች ........................................................................... 30

## የሕብረት ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር የተሻሻለ

## መመሥረቻ ጽሑፍ

### አንቀጽ አንድ

### የዚህ ሠነድ ዓላማ

ሕብረት ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር (ከዚህ በኋላ አክሲዮን ማህበር/ማሕበሩ በመባል ይጠቀሳል) በ1952 ዓ.ም. የወጣው የንግድ ሕግ በሚደነግገው መሠረት በቁጥር 170/4/87 እና 171/4/87 በ1987 ዓ.ም. የተመዘገቡ የመመሥረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ እንዲኖሩት ሆኖ በ1987 ዓ.ም. ተመሥርቷል፡፡

በ2013 ዓ.ም. የወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ (ከዚህ በኋላ የንግድ ሕግ ተብሎ ይጠቀሳል) የመተዳደሪያ ደንብ ተብሎ ይታወቅ የነበረውን ሠነድ በግልፅ እውቅና ያልሰጠው እና በ1952 ዓ.ም. የወጣው የንግድ ሕግ ላይ በመተዳደሪያ ደንብ ላይ ይወሰናሉ የሚባሉ ጉዳዮችን በመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ ይወሰናሉ በማለቱ አክሲዮን ማሕበሩ ያለውን የመተዳደሪያ ደንብ ከመመሥረቻ ጽሑፍ ጋር በማዋሃድ፣ የንግድ ህጉ ካመጣቸው ሌሎች ለውጦች ጋር በማስማማት እና ነባራዊ ለውጦችን በመውሰድ መመሥረቻ ጽሑፍን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም፣ የአክሲዮን ማሕበሩ የባለአክሲዮኖች 14ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ይህን የተሻሻለ መመሥረቻ ጽሑፍ አጽድቋል፡፡ ይህ ሰነድ የሕብረት ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር የተሻሻለ መመሥረቻ ጽሁፍ ተብሎ ይጠራል፡፡ (በዚህ ሠነድ በነጠላ ቁጥር የተጠቀሰው አግባብነት ሲኖረው ለብዙም ያገለግላል፡፡ በወንድ ፆታ የተጠቀሰው አግባብነት ሲኖረው ለሴት ፆታም ያገለግላል፡፡)

### ምዕራፍ አንድ

### የአክሲዮን ማሕበሩ አደረጃጀት፣ ዓላማዎች እና ባለአክሲዮኖች

### አንቀት ሁለት

### የአክሲዮኑ ማህበሩ ስም

የአክሲዮን ማህበሩ “ሕብረት ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር” በመባል ይታወቃል፡፡

## <u>አንቀት ሦስት</u>

## <u>የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ፣ ቅርንጫፎች እና ተቀጥላ ማህበራት</u>

3.1. የሕብረት ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር ዋና መ/ቤት አድራሻ ኢትዮጵያ፣ አዲስ አበባ ከተማ፣ አራዳ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 02 ፣ የቤት ቁጥር 220 ሕብረት ኢንሹራንስ ህንጻ ሲሆን አድራሻው እንደ አስፈላጊነቱ ሊቀየር ይችላል።

3.2. ሕብረት ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር በኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፎችና አገናኝ ቢሮዎች ያሉት ሲሆን፣ በአክሲዮን ማሕበሩ ማኔጅመንት ውሳኔ መሠረት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና ተገቢውን ፈቃድ ከሚመለከተው አካል ሲያገኝ በኢትዮጵያ ተጨማሪ ቅርንጫፎች፣ አገናኝ ቢሮዎች እንዲሁም ከኢትዮጵያ ውጭ ቅርንጫፎች እንዲሁም ተቀጥላ ማህበራት /Subsidiaries/ ሊከፍት ይችላል።

## <u>አንቀጽ አራት</u>

## <u>የአክሲዮን ማህበሩ የንግድ ዓላማዎችና የሥራ መስክ</u>

አክሲዮን ማሕበሩ የሚከተሉት ዓላማዎች እና የሥራ መስኮች ይኖሩታል።

4.1 የረጅም ጊዜ መድን ስራ ለመስራት

4.2 የጠቅላላ መድን ሥራ ለመስራት

4.3 ማንኛውንም የመድንና የጠለፋ መድን ሥራዎችን በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያም ውጭ ማከናወን፣

4.4 አክሲዮን ማህበሩ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ በሌሎች መድን ወይም የጠለፋ መድን ሥራ መካፈል፣

4.5 ለሌሎች የመድንና የጠለፋ መድን ማህበራት ወኪል ወይም ተጠሪ ሆኖ መስራት፣

4.6 ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ተመሳሳይ ወይም ከላይ የተጠቀሱት ሥራዎች ተጓዳኝ የሆኑን ማንኛውንም ንግድ እንዲሁም ከኢንቨስትመንት ዓላማ ጋር የተገናኙ እና/ወይም የንግድ ዓላማውን ለማራመድ የሚረዱ የንግድ ሥራዎችን ማከናወን፣

4.7 በኢንቨስትመንት የማማከርና ሀብት የማስተዳደር አገልግሎቶችን መስጠት፣

4.8 በሪል እስቴት የድለላ አገልግሎት መስጠት፣

4.9 በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙና አክሲዮን ማሕበሩ ከፍተኛ የባለቤትነት ድርሻ ለያዘባቸው ድርጅቶች መረጃ የማጠናቀር አገልግሎት የመስጠት፤

4.10 አክሲዮን ማህበሩ ከሚያራምደው የመድን ሥራ አይነት ጋር በተያያዘ ለመድን ወኪሎች እና ለመድን ደላሎች እገዛ ማድረግ፤

4.11 ንብረት በአደራ የማስቀመጥ ተግባር ማከናወን፣

4.12 የኢንቨስትመንት-መድን ቁርኝት አገልግሎት መስጠት፤

4.13 አክሲዮን ማሕበሩ ከሚያካሂዳቸው የመድን ሥራዎች ጋር በተያያዘ የአደጋ ሥጋት አስተዳደርና ጉዳት የማስተካከያ ምክር አገልግሎት መስጠት፤

4.14 አክሲዮን ማሕበሩ ከሚያካሂደው የመድን ሥራ ጋር በተያያዘ ለመድን ወኪሎችና ለመድን ደላላዎች መረጃዎችን የማጠናቀር አገልግሎት የመስጠት፤

4.15 አክሲዮን ማሕበሩ ከሚያካሂደው የመድን ሥራ ዓይነት ጋር በተያያዘ ለመድን ወኪሎችና ለመድን ደላሎች እገዛ የማድረግ፣ እና

4.16 አክሲዮን ማሕበሩ ከሚያካሂደው የመድን ሥራ ጋር በተያያዘ የባለሞተር ተሽከርካሪ ጥገናና ጉዳት ግምት አገልግሎት የሚሰጥበት ጋራጅ ማቋቋምና ማካሄድ፤

4.17 ሕግ በሚፈቅደው በኢንቬስትመንት የሰራውን ሕንፃ ማከራየት፤

4.18 ሕግ በሚፈቅድለት የካፒታል ገበያ መስኮች መሰማራት፤

4.19 በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም ሌላ አግባብነት ያለው የመንግስት አካል እና ሕግ በሚፈቅደው የኢንቬስትመንት መስክ መሠማራት ናቸው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የአክሲዮን ማሕበሩ ካፒታል፣ ከአክሲዮን የሚመነጩ የባለአክሲዮኖች መብቶችና ግዴታዎች

### አንቀጽ አምስት

### የአክሲዮን ማህበሩ ዋና ገንዘብ /ካፒታል/

5.1. የአክሲዮ ማህበሩ የተፈረመ ካፒታል ብር 1,500,000,000.00 /አንድ ቢሊዮን አምስት መቶ ሚሊዮን ብር ነው/ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የተፈረመ ካፒታል እያንዳንዳቸው ብር 1,000.00 /አንድ ሺ/ ዋጋ ባላቸው 1,500,000.00 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ) ተራና የተመዘገቡ አክሲዮኖች የተከፋፈለ ነው፡፡ ከተፈረመው ካፒታል ውስጥ ብር 1,068,175,000(አንድ ቢሊዮን ስልሳ ስምነት ሺ አንድ መቶ ሰባ አምስት ብር) በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል፡፡

### አንቀጽ ስድስት

## የአክሲዮን ይዞታ ገደብ

6.1. አንድ አዲስ ባለአክሲዮን ሊገዛ የሚችለው አነስተኛ የአክሲዮን ብዛት 50 አክሲዮን ወይም ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺ ብር) ዋጋ ያላቸው አክሲዮኖችን ነው።

6.2. በተራ ቁጥር 6.1 የተገለፀው ገደብ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣ በውርስ፣ በስጦታ፣ ለአክሲዮን ማሕበሩ ሠራተኞች ወይም ለነባር ባለአክሲዮኖች የሚደረግ ዝውውርን አይመለከትም።

6.3. ማንኛውም ባለአክሲዮን ከተፈረመው ካፒታል ውስጥ ሕግ በሚፈቀደው ሁኔታና መጠን ያህል መያዝ ይችላል።

## አንቀጽ ሰባት

## የአክሲዮኖች ዓይነትና መደብ

የአክሲዮን ማህበሩ አክሲዮኖች እኩል ዋጋ ያላቸው ሙሉ ለሙሉ በጥሬ ገንዘብ የሚከፈሉ አንድ ዓይነት እኩል፣ ልዩ መብት የማይሰጡ የተመዘገቡና ተራ አክሲዮኖች ናቸው።

## አንቀጽ ስምንት

## የባለአክሲዮኖች ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፤ የፈረሙትን የአክሲዮን ብዛትና የተከፈለውን የገንዘብ መጠን ዝርዝር

ይህ ሰነድ ሲዘጋጅ ያሉ የአክሲዮን ማሕበሩ ባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝር፤ አድራሻቸው፤ ዜግነታቸውን፤ የፈረሙት አክሲዮን ብዛትና የከፈሉትን የአክሲዮን ዋጋ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ከዚህ የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽሑፍ ጋር አባሪ ሆኗል።

## አንቀጽ ዘጠኝ

## የአክሲዮኖች አከፋፈልና ቀሪ ዋጋቸው ላልተከፈለ አክሲዮኖች ስለሚኖር ኃላፊነት

9.1 የአክሲዮን ማሕበሩ ባለአክሲዮኖች አዲስ አክሲዮን ለመግዛት በፈረሙ ጊዜ ቢያንስ የተፈረሙትን አክሲዮኖች 25% ወዲያውኑ መክፈል አለባቸው። አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አዲስ አክሲዮን ግዢ በሚፈፀምበት ጊዜ ወዲያዉኑ መከፈል የሚኖርበትን የገንዘብ መጠን ከ25% በመጨመር ሊወስን ይችላል።

9.2 ተፈርሞ ያልተከፈለ ቀሪ የአክሲዮን ዋጋ የሚከፈልበት ጊዜ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው የሚወሰን ይሆናል።

9.3 የአክሲዮን ማሕበሩ ባለአክሲዮኖች፤ አክሲዮኑ ቀደም ሲል ተላልፎላቸው የነበሩ ሰዎች እንዲሁም አክሲዮኑን ከአክሲዮን ማህበሩ ለመግዛት የፈረሙ ሰዎች በተፈረሙ አክሲዮኖች ላይ ላላተከፈለው ቀሪ ገንዘብ ክፍያ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

9.4 አክሲዮኖቹ የተሰጡት በአላባ ጥቅም እንደሆነ፤ ባለአላባው የአላባው ጊዜ መብት ሲያልቅ የከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት ለመጠየቅ ያለው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ባልተከፈለ የአክሲዮን ገንዘብ ጥሪው መሠረት ቀሪው ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

9.5 ዋጋቸው ያልተከፈለ አክሲዮኖች ቀሪ ሂሳብ እንዲከፈል ጥሪ ከተሰጠ በኃላ ይህንኑ በተወሰነው ቀን ካልተከፈለ የንግድ ሕግ አንቀጽ 289 ከንዑስ አንቀጽ 3 እስከ 7 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## <u>አንቀጽ አስሥር</u>

## <u>ከአክሲዮን ይዞታ የሚመነጩ የባለአክሲዮኖች መብቶችና ግዴታዎች</u>

10.1 አግባብ ያላቸው ሕጐችና ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ አክሲዮኖች ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን የሚከተሉትን መብቶች ያሰጣሉ፡፡

10.1.1 በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የመገኘት፣ የመሳተፍ እና ድምጽ የመስጠት፤

10.1.2 በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚጸድቀውን የትርፍ ድርሻ በከፈሉት የአክሲዮን መጠን ልክ የማግኘት፤

10.1.3 በሕግ መሠረት ድምጽ የመስጠት መብትን የሚያሳጡ ሁኔታዎች ከሌሉ በስተቀር በእያንዳንዱ አክሲዮን አንድ ድምጽ የመስጠት መብት፤

10.1.4 ካፒታል ለመጨመር በጥሬ ገንዘብ የሚሸጥ አዲስ አክሲዮኖች በሚወጡበት ጊዜ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን አስቀድሞ በያዛቸው አክሲዮኖች መጠን ልክ አዲስ አክሲዮን የመግዛት ቅድሚያ የማግኘት፤

10.1.5 ቃለ-ጉባኤዎችን እና ጠቅላላ ስብሰባዎች ላይ የተገኙ አባላትን ስም ዝርዝር የመመልከት መብት እንዲሁም የሀብትና ዕዳ ሚዛን፤ የትርፍና የኪሣራ ሂሳብ፤ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና የኦዲተሮች ሪፖርቶችን ቅጅዎች የመውሰድ፤

10.1.6 አክሲዮን ማህበሩ በመክሰር ወይም በሌላ ምክንያት ሥራ በሚያቆምበትና ንብረቱ በሚጣራበት ጊዜ ለካፒታል ባስገባው መዋጮ መጠን ተሰልቶ ከተረፈው ንብረት ላይ ድርሻውን የማግኘት፤

10.1.7 በዚህ ንዑስ አንቀጽ 10.1.4 የተመለከተውን መብት የሚያስገኙት ዋጋቸው በሙሉ በተከፈሉ አክሲዮኖች ብቻ ናቸው፡፡

10.2 የባለአክሲዮኖች ግዴታዎች፤ በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍና አግባብነት ባላቸው ሕጐችና ድንጋጌዎች መሠረት የሚመሩ ሆኖ፤ ባለአክሲዮኖች ለማህበሩ ዕዳ ወይም ግዴታ ተጠያቂ የሚሆኑት በስማቸው በያዟቸው አክሲዮኖች ዋጋ መጠን ልክ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አሥራ አንድ

## የአክሲዮን የጋራ ባለቤቶች መብትና ኃላፊነት

11.1 ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች አክሲዮን በጋራ መግዛት ይችላሉ፡፡ እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ የባለአክሲዮንነት መብታቸውን የሚጠቀሙት የጋራ ወኪል በመሾም ነው፡፡

11.2 የጋራ ወኪል ባልሾሙ ጊዜ ማህበሩ ለአንዱ ባለአክሲዮን የጋራ ባለቤት የሚሰጠው ማስታወቂያ ወይም መግለጫ ለቀሪዎቹ የአክሲዮኑ የጋራ ባለቤቶችም ጭምር እንደተሰጠ ይቆጠራል፡፡

11.3 የአክሲዮን የጋራ ባለቤቶች ከባለአክሲዮንነት ለሚመነጩ ኃላፊነቶች በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ ናቸው፡፡

## አንቀጽ አሥራ ሁለት

## በመያዣ ወይም በአላባ ስለሚሰጡ አክሲዮኖች

12.1 የተለየ ስምምነት በሌለ ጊዜ፤ አክሲዮኖቹ በመያዣ ወይም በአላባ ጥቅም የተሰጡት እንደሆነ ማህበሩ ጉባዔዎች ድምፅ የመስጠት መብት የሚኖረው አክሲዮኑን በመያዣ የያዘው ወይም የአላባ ጥቅም ያለው ሰው ነው፡፡

12.2 ለነባር ባለአክሲዮኖች አዲስ አክሲዮን ለመግዛት በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ የተቀመጠው የቅድሚያ የመግዛት መብት የባለአክሲዮኑ ሆኖ ይቀጥላል፡፡

12.3 በመያዣ ለተሰጠ አክሲዮን የሚከፈል ቀሪ ገንዘብ መክፈል ያለበት ባለአክሲዮኑ ነው፡፡

## አንቀጽ አሥራ ሦስት

## የባለአክሲዮኖች መዝገብ

13.1 አክሲዮን ማህበሩ የባለአክሲዮኖችን መዝገብ መያዝ አለበት፡፡ መዝገቡ በአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት መያዝ ያለበት ሲሆን፤ በወረቀት ወይም ለረዥም ዘመን በሚቆይ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ መያዝ ይችላል፡፡

13.2 መዝገቡ የባለአክሲዮኖችን ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የአክሲዮኖች ብዛትና መለያ ቁጥር፣ የተከፈለውንና ያልተከፈለውን ገንዘብ መጠን እንዲሁም ባለአክሲዮኖቹ የተመዘገቡበትን ቀን መያዝ አለበት፡፡

13.3 መዝገቡ ማንኛውም ባለአክሲዮን እና ማንኛውም በሕግ የተፈቀደለት ሰው ሊመለከተው እንዲችል ሆኖ በአክሲዮን ማሕበሩ ዋና መሥሪያ ቤት ለረጅም ጊዜ በሚቆይ መልኩ በወረቀት ሠነድ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ተይዞ በመደበኛ የሥራ ሰዓታት ሁሉ ክፍት ሆኖ ይቀመጣል፡፡

13.4 መዝገቡን ባለአክሲዮኖች እና ማንኛውም በሕግ የተፈቀደለት ሰው የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም የመዝገቡን ግልባጭ ወይም በአጭር የተውጣጣ ጽሑፍ እንዲሰጠው አክሲዮን ማህበሩን መጠየቅ ይችላል፡፡

## <u>አንቀጽ አሥራ አራት</u>

## <u>አክሲዮኖችን ለሌላ ወገን ስለማስተላለፍ</u>

14.1 አክሲዮኖች ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ያለምንም ገደብ ይተላለፋሉ፡፡ በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 6 እና አግባብነት ያላቸው ገደቦች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

14.2 አክሲዮኖች ለሌላ ወገን በሚተላለፉበት ጊዜ ይኸው ሁኔታ በባለአክሲዮኖች መዝገብ ላይ መመዝገብ ያለበት ሲሆን በባለአክሲዮኖች መዝገብ ላይ ካልተጻፈ በስተቀር የአክሲዮን መብት ለተላለፈለት ሰው የተሟላ ሆኖ አይቆጠርም፡፡ የአክሲዮን ዝውውርም ዋጋ አይኖረውም፡፡

14.3 አክሲዮኖችን በጋራ ከያዙ ባለአክሲዮኖች መካከል አንዱ ቢሞት የሟች የአክሲዮን ድርሻ ላይ መብት የሚኖራቸው በሕይወት የሚገኘው (የሚገኙት) የሟቹ ወራሽ /ወራሾች/ ይሆናሉ፡፡

14.4 አክሲዮኖች በጋራ የያዙ ባለአክሲዮኖች የባለአክሲዮንነት መብታቸውን መጠቀም የሚችሉት የጋራ ወኪል በመሾም ሲሆን ከባለአክሲዮንነት ለሚመነጩ ኃላፊነቶች በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂዎች ናቸው፡፡

14.5 ማንኛውንም ሰው ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን ሊያደርግ የሚችል የአክሲዮን ዝውውር በአክሲዮን መዝገብ ከመመዝገቡ በፊት በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት።

## ምዕራፍ ሦስት

## የአክሲዮን ማህበሩ የሥራ አመራር አካላት እና ሥልጣን

### አንቀጽ አሥራ አምስት

### የአክሲዮን ማህበሩ የሥራ አመራር አካላት

የአክሲዮን ማህበሩ የሥራ አመራር አካላት የሚከተሉት ናቸው።

1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ፣
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ፣
3. ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣
4. የውጪ ኦዲተር/ሮች
5. የማሕበሩ ፀሐፊ ናቸው

### አንቀጽ አሥራ ስድስት

### የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ

16.1 የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ መደበኛ ወይም አስቸኳይ ይሆናሉ።

16.2 መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኦዲተሮች በሚያደርጉት ጥሪ መሠረት የበጀት ዓመቱ በተዘጋ በስድስት ወራት ውስጥ በዓመት አንድ ጊዜ መደረግ አለበት። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔዎች ሊደረጉ ይችላሉ።

16.3 የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ የሚያደርጉት እንደነገሩ ሁኔታ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ ኦዲተሮች፣ ሒሳብ አጣሪዎች ወይም ፍርድ ቤት ናቸው።

16.4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 16.2 ሥር የተመለከተው ቢኖርም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ወይም አግባብ ያለው ሌላ የመንግስት አካል ጉዳዩ አንገብጋቢ ሆኖ ሲያገኘው እና በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 16.2 መሠረት ስብሰባ መጥራት የማይቻል ወይም ረጅም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ በጉዳዩ ያገባኛል በሚል ማንኛውም ሰው ጥያቄ ወይም በራሱ ተነሳሽነት ጉባዔ ሊጠራ ይችላል፤ ሆኖም ጉባዔው

እንዲጠራ ጥያቄ የቀረበው የአክሲዮን ማሕበሩ ዋና ገንዘብ አሥር በመቶ ወይም ከዚያ በላይ በሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ከሆነ የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ወይም አግባብ ያለው ሌላ የመንግሥት አካል ጉባዔ የመጥራት ግዴታ አለበት፡፡

16.5 ከአክሲዮን ማሕበሩ ዋና ገንዘብ ቢያንስ አምስት በመቶ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች የአክሲዮን ማሕበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት ቦታ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡና ፍርድ ቤቱ ጥያቄው ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን ጠቅላላ ጉባዔ እንዲሰበሰብ ጥሪ የሚያደርግና አጀንዳ የሚያዘጋጅ ተወካይ ሊሰይም ይችላል፡፡

16.6 በጠቅላላ ጉባዔ ላይ ባለአክሲዮኖች በአካል በመገኘት ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም ሁሉም ባለአክሲዮኖች የተስማሙ እንደሆነ ስብሰባ ማድረግ ሳያስፈልግ ለውሳኔ በቀረበ ጉዳይ ላይ ሃሳባቸውን በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመግለጽ ውሳኔ ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡

## <u>አንቀጽ አሥራ ሰባት</u>

## <u>የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር</u>

17.1 የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የአክሲዮን ማህበሩ የበላይ አካል ነው፡፡

17.2 የባለአክሲዮኖች የተለያዩ ዓይነት ጠቅላላ ጉባዔዎች በንግድ ሕግና በዚህ የአክሲዮን ማህበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ በተወሰነው መሠረት ይካሄዳል፡፡

17.3 በንግድ ሕግና አግባብነት ባላቸው የመድን ሥራ ሕጐች ውስጥ የተደነገገው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው እንደአስፈላጊነቱ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል፡-

17.3.1 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ይሾማል፣ ይሽራል፣ ክፍያቸውንም ይወስናል፤

17.3.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ይሾማል፤ ይሽራል፤ ክፍያቸውንም ይወስናል፤

17.3.3 የአክሲዮን ማሕበሩን የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ፤ የትርፍና ኪሣራ ሂሳብ መግለጫ እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድን ሪፖርት፣ የኦዲተሮችን ሪፖርት አድምጦ የማሻሻል ወይም የማጽደቅ፤ ወይም ያለመቀበል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በትርፍ አመዳደብ እና አከፋፈል እንዲሁም በአጠቃላይ ያለፈውን የሂሳብ ዓመት ማጠቃለያ የተመለከቱ የሂሳብ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ያስተላልፋል፣

17.3.4 የአክሲዮን ማሕበሩን የውጭ ኦዲተሮች ይሰይማል፣ ይሽራል፤ የሥራ ጊዜያቸውንና የሚከፈላቸውንም ክፍያ ይወስናል፤

17.3.5 በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ወይም አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲወስንባቸው ተለይተው ከተቀመጡት ውጭ ያሉ ጉዳዮች ላይ ጠቅላላ ጉባዔው ይወስናል።

17.4 አግባብነት ባላቸው ሕጐች እና በንግድ ሕግ ውስጥ የተደነገገው የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔው እንደአስፈላጊነቱ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል።

17.4.1. የመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ ማሻሻያዎችን ያደርጋል፤

17.4.2. የአክሲዮን ማሕበሩን ዓላማዎች ያሻሽላል፤

17.4.3. የአክሲዮን ማሕበሩን ዋና ካፒታል ይቀንሳል ወይም ይጨምራል፤

17.4.4. አክሲዮን ማሕበሩ እንዲፈርስና ሂሳቡም እንዲጣራ ይወስናል፤

17.4.5. አክሲዮን ማሕበሩ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ሌላ አክሲዮን ማሕበር ወይንም የፋይናንስ ተቋም ወይንም ድርጅት ጋር እንዲጠቃለል፣ ከሌላ መድን ሰጪ ወይንም የፋይናንስ ተቋም ወይንም ድርጅት ጋር እንዲዋሀድ ወይም እንዲከፋፈል ሊወስን ይችላል።

17.5 ለጉባዔው ዓይነትና የአጀንዳ ነጥብ እና በሕግ የሚጠየቀው ምልዓተ ጉባዔ እንደተጠበቀ ሆኖ በጠቅላላ ጉባዔ የተላለፉ ውሳኔዎች በሁሉም ባለአክሲዮኖች፣ በባለአክሲዮኖች በሙሉ በመወከል በስብሰባ ባልተገኙት፣ በሀሳብ በተለዩት፤ በውሳኔው ባልተስማሙ፣ ድምጽ ባልሰጡ ወይም ለመስጠት በማይችሉ ባለአክሲዮኖች ላይ ጭምር ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

17.6 ከላይ በንዑስ አንቀፅ 17.5 የተደነገገው ቢኖርም ባለአክሲዮኑ ራሱ ካልተስማማ በስተቀር ባለአክሲዮኑ አባል በመሆኑ ምክንያት ሊያገኝ የሚገባውን መሠረታዊ መብት ጠቅላላ ጉባዔው ሊነፍገው አይችልም።

## <u>አንቀጽ አሥራ ስምንት</u>

## <u>የጠቅላላ ጉባዔዎች የጥሪ ማስታወቂያ እና በባለአክሲዮን መዝገብ ስለመጻፍ</u>

18.1 ጠቅላላ ጉባዔ መጥራት በሚያስፈልግበት ጊዜ ከስብሰባው ዕለት 24 (ሃያ አራት) ቀናት አስቀድሞ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ የስብሰባው ጥሪ መተላለፍ አለበት። ወይንም

ስብሰባው በአክሲዮን ማሕበሩ ወጪ በተመዘገበ ደብዳቤ ወይም የኢሜይል አድራሻ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊጠራ ይችላል፡፡

18.2 የጥሪ ማስታወቂያው በፖስታ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን የሚተላለፍ ቢሆንም ስብሰባውን በሚጠራው አካል ውሳኔ መሠረት ጥሪው በተጨማሪ በጋዜጣ ሊደረግ ይችላል፡፡

18.3 ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 18.1 እና 18.2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሌላ ማስታወቂያ ለባለአክሲዮኑ የሚተላለፍለት በአስመዘገበው አድራሻ መሠረት እንደአመቺነቱ በመልዕክተኛ፣ በፖስታ፣ በፋክስ፣ በኢሜል፣ በስልክ የጽሑፍ መልዕክት ወይም በሬዲዮ ወይም በጋዜጣ ሊሆን ይችላል፡፡

18.4 ማንኛውም የአክሲዮን ባለሀብት በባለአክሲዮኖች መዝገብ ውስጥ መጻፍ የሚችለው ጠቅላላ ጉባዔው ከሚደረግበት ቀን 10 የሥራ ቀናት አስቀድሞ ነው፡፡ ይህ ሁኔታም የጥሪ ማስታወቂያው ላይ ይገለጻል፡፡

## አንቀጽ አሥራ ዘጠኝ

## ውክልና

19.1 የውክልና ሠነዶች ጠቅላላ ጉባዔ ከሚደረግበት ዕለት ሦስት ቀን አስቀድሞ ለአክሲዮን ማሕበሩ ዋና መ/ቤት መቅረብ አለባቸው፡፡

19.2 በጉባዔው ላይ ለመገኘት የሚያስችል የውክልና ይዘት፣ ተሞልተው የሚላኩበት የጊዜ ገደብና ቦታው በዳይሬክተሮች ቦርድ ተወስኖ በጥሪው ማስታወቂያ ላይ መገለጽ አለበት፡፡

19.3 አንድ ባለአክሲዮን የአክሲዮን ማሕበሩ ባለአክሲዮን በሆነ ወይም ባልሆነ ሰው ሊወከል ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሃያ

## የጥቅም ግጭት

20.1 በራሱ ስም ወይም ሌላ ሦስተኛ ወገንን ወክሎ በጉባዔ ላይ የሚገኝ ተሳታፊ ከአክሲዮን ማሕበሩ ጥቅሞች ጋር የሚጋጭ ጥቅም ያለው ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ተሳታፊው በቀረበው ጉዳይ ላይ ድምጽ የመስጠት መብት አይኖረውም፡፡

20.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የራሳቸውን ኃላፊነትና ግዴታ በሚመለከት ውሳኔ ላይ ድምጽ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፡፡

20.3 ምልዓተ-ጉባዔ በሚሰላበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ መሠረት ድምፅ የመስጠት መብት የተነፈጋቸው አክሲዮኖች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ ሃያ አንድ

## መደበኛና አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች ለማካሄድ ስለሚያስፈልገው ምልዓተ-ጉባዔ እና ውሳኔ የሚተላለፍበት ድምጽ

21.1 መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፡- በመደኛ ጠቅላላ ጉባዔ የመጀመሪያ ጥሪ፣ ድምጽ የመስጠት መብት ከሚሰጡ የአክሲዮን ማሕበሩ አክሲዮኖች ቢያንስ አንድ አራተኛ (1/4) የያዙ ባለአክሲዮኖች ራሳቸው ወይም እንደራሴዎቻቸው መገኘት አለባቸው፡፡ በሁለተኛው ጥሪ የተወከሉት ድምጽ የመስጠት መብት የሚሰጡት አክሲዮኖች ቁጥር የትኛውንም ያህል ቢሆን፣ ጉባዔው ስብሰባውን ለማካሄድና ውሳኔ ለማስተላለፍ ይችላል፡፡ ጉባዔው ላይ ድምጽ ተአቅቦዎችን እና ባዶ ድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ከግምት ውጭ በማድረግ በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች የሚጸድቁት በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡

21.2 አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ፡- የኢንሹራንሱ ዜግነት እንዲለወጥ የሚያደርጉ ወይም በነባር አክሲዮኖች ላይ የተጻፈውን ዋጋ በመጨመር የአክሲዮን ማሕበሩን ካፒታል ከፍ እንዲደረግ የሚጠይቁ ውሳኔዎች ሁሉ ዋጋ ሊኖራቸው የሚችለው ድምጽ ለመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች የያዙ ባለአክሲዮኖች በአስቸኳይ ጉባዔው ላይ ተገኝተው ወይም ተወክለው በሙሉ ድምፅ ሲስማሙበት ብቻ ይሆናል፡፡ በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 21.2.1 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም አስቸኳይ ጉባኤ ላይ ውሳኔዎች በሁለት ሶስተኛ (2/3ኛ) አብላጫ ድምጽ የሚጸድቁ ሆኖ በሚከተለው መሠረት አፈጻጸሙ ይወሰናል፡፡ ለድምጽ ብልጫው አቆጣጠር ስሌት ድምጽ ያልሰጡም ሆነ ድምጽ ያልተጻፈባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ግምት ውስጥ አይገቡም፡፡ በመጀመሪያ ጉባዔ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ከአንድ ሶስተኛ (1/3) ያላነሱትን የያዙ ባለአክሲዮኖች ሲገኙ፣ ወይም ሲወከሉ፣ በሁለተኛው ጉባዔ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው የተፈረሙ አክሲዮኖችን ከአንድ አራተኛ (1/4) ያላነሱ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖችን የያዙ ባለአክሲዮኖች ሲገኙ ወይም ሲወክሉ፣ በሦስተኛው ጉባኤ የወከሉት ድምጽ የመስጠት መብት የሚሰጡት አክሲዮኖች ቁጥር የትኛውንም ያህል ቢሆን፣ ጉባዔው ስብሰባውን ለማካሄድና ውሳኔ ለማስተላለፍ ይችላል፡፡

21.3 ሕግንና ይህን የመመሥረቻ ጽሑፍን በመተላለፍ በመደበኛም ሆነ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በተሰጡ ውሳኔዎች ጥቅሙ የተጎዳ ሰው፣ ውሳኔዎቹ ከተሰጡበት ቀን ጀምሮ በዘጠና ተከታታይ ቀናት ውስጥ መቃወሚያ ሊያቀርብባቸው ይችላል። የአንድ ጉባዔ ውሳኔ እንዲሻር ወይም እንዲሰረዝ የሚቀርበው መቃወሚያ ላይ የንግድ ሕግ አንቀጽ 391 ንዑስ አንቀጽ (2-7) ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## <u>አንቀጽ ሃያ ሁለት</u>

## <u>የጠቅላላ ጉባዔ ቃለጉባዔዎች</u>

22.1 በጠቅላላ ጉባዔዎች ላይ የሚደረጉ ውይይቶች በቃለ-ጉባዔ መያዝ አለባቸው። ቃለ-ጉባዔዎች በስብሰባው ላይ በተገኙት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና በአክሲዮን ማህበሩ ፀሐፊ ይፈረማሉ።

22.2 ቃለ-ጉባዔ ወደ መዝገብ በትክክል ስለመገልበጡ በአክሲዮን ማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም በሌሎች ሁለት የቦርድ አባላት መረጋገጥ አለበት።

22.3 የጠቅላላ ጉባዔ ቃለ-ጉባዔዎች በተለይ ከዚህ በታች የመለከቱትን ጉዳዮች መያዝ አለባቸው።

22.3.1 የጉባዔውን ጥሪ አደራረግ፤

22.3.2 የስብሰባውን ቦታና ቀን፤

22.3.3 አጀንዳዎቹን፤

22.3.4 በጉባዔው የተገኙ የቦርድ አባላትን ስም፤

22.3.5 በስብሰባው ላይ የተገኙ አክሲዮኖችን ብዛትና የምልዓተ ጉባዔውን ቁጥር፤

22.3.6 ለጉባዔው የቀረቡትን ሠነዶች፤

22.3.7 የውይይቱን አጭር ማጠቃለያ፤

22.3.8 የተሰጡትን ድምጾች ውጤት እና

22.3.9 ጉባዔው ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች፤

## <u>አንቀጽ ሃያ ሦስት</u>

## <u>የዳይሬክተሮች ቦርድ መሰየም እና የሥራ ዘመን</u>

23.1 አክሲዮን ማሕበሩ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በሚመረጡ የዳይሬክተሮች ቦርድ ይመራል፡፡ በቦርድ አባልነት ሊሾሙ የሚችሉት ዳይሬክተሮች ባለአክሲዮኖች የሆኑ ብቻ ናቸው፡፡

23.2 የዳይሬክተሮች የሥራ ዘመን ሦስት (3) ዓመት ነው፡፡ ዳይሬክተሮቹ በየ3 /በየሶስት/ ዓመቱ ይመረጣሉ፡፡

23.3 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥራ ተከታታይነት እንዲኖረው በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ሲወሰን በየምርጫው ለሁለት ተከታታይ የሥራ - ዘመን ካገለገሉ ነባር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ውስጥ ቢበዛ 1/3ኛ /አንድ ሦስተኛው/ ለሦስተኛ የሥራ-ዘመን እንደገና መመረጥ ይችላሉ፡፡ እንደገና የተመረጡት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ለአንድ የቦርድ የሥራ ዘመን ብቻ ያገለግላል/ሉ፡፡

23.4 በአንቀጽ 23.3 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ከስድስት ተከታታይ ዓመታት በላይ በዳይሬክተርነት ማገልገል አይችልም፡፡ ሆኖም የዳይሬክተሩ አገልግሎት ካበቃ ከ6 (ስድስት ዓመታት በኋላ እንደገና መመረጥ ይችላል፡፡

23.5 ጠቅላላ ጉባዔው በሕጉ እና በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ በተገለፀው መሠረት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን በማናቸውም ጊዜ የማሰናበት ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው፣ የ3 (ሦስት) ዓመት የሥራ ዘመን ከማለቁ በፊት ከ50% በላይ ዳይሬክተሮች የሥራ ስንብት ሲያቀርቡ አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ ጠቅላላ ጉባዔውን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

23.6 ዳይሬክተሮቹ ሥራቸውን ሲለቁና አዲስ ለተመረጡት ዳይሬክተሮች ሥራቸውን ማስተላለፍ የሚችሉት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ካገኙ በኋላ ነው፡፡ በዚህ አንቀጽ መሠረት እስከሚተኩ ድረስ ነባር ዳይሬክተሮች አክሲዮን ማሕበሩን የማገልገል ግዴታ አለባቸው፡፡

23.7 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አዲስ የተመረጡ ዳይሬክተሮችን ሹመት በጽሑፍ እስኪያጸድቅ ድረስ የነባር ዳይሬክተሮች የሥራ ዘመን ሳይቋረጥ ይቀጥላል፡፡

23.8 ቦርዱ ከአባላቱ መካከል ሊቀመንበር ይመርጣል፡፡

## <u>አንቀጽ ሃያ አራት</u>

## <u>የቦርድ አባላት ቁጥር</u>

24.1 አክሲዮን ማሕበሩ 9 /ዘጠኝ/ የቦርድ አባላት /ዳይሬክተሮች ይኖሩታል፡፡

## አንቀጽ ሃያ አምስት

## ለማህበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ

25.1 አክሲዮን ማሕበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 311 መሠረት ይይዛል፡፡

25.2 ባለአክሲዮኖች እና የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተወካዮች መዝገቡን በነጻ ማየት ይችላሉ፤ ባለአክሲዮን ያልሆኑ ሰዎች ለዚሁ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈጸም መዝገቡን የማየት መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ ሃያ ስድስት

## የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣንና ተግባር

26.1 የዳይሬክተሮች ቦርድ አግባብነት ባላቸው ሕጐች፣ በአክሰዮን ማሕበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ እና በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች የተሰጠ ወይም የሚሰጥ ተግባርና ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

26.2 በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ወይም በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት ለሌላ አካል በሕግ ተለይቶ የተሰጠ ካልሆነ በስተቀር ለአክሲዮን ማሕበሩ የተሰጡ ሥልጣኖች ሁሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣኖች ይሆናሉ፡፡

26.3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 26.1 የተጠቀሰው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል፡፡

26.3.1 የአክሲዮን ማህበሩን ሥራ አመራር ይቆጣጠራል፡፡

26.3.2 የአክሲዮን ማህበሩን ዋና የሥራ አስፈፃሚ፤ የውስጥ ኦዲት ኃላፊና የሪስክና ኮምፕሊያንስ ኃላፊን መርጦ ይሾማል፡፡

26.3.3 የዋና ሥራ አስፈፃሚ ምክትል የሆኑ ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎች /ሲኒየር ኤክስኪዩቲቭ ኦፊሰሮች/ በዋና ሥራ አስፈፃሚ ተመርጠው ሲቀርቡለት ሹመታቸውን ያጸድቃል፡፡

26.3.4 የአክሲዮን ማህበሩን ጸሐፊ ቅጥርና ስንብት በዋና ሥራ አስፈፃሚ ሲቀርብለት ሹመቱን ያጸድቃል፡፡

26.3.5 የአክሲዮን ማህበሩን ስትራቴጂዎችን፣ ፖሊሲዎችን፣ ሲስተሞችንና ዓመታዊ ዕቅድና በጀት በዋና ሥራ አስፈፃሚው ተዘጋጅተው ሲቀርቡለት በአግባቡ ተመልክቶና ከልሶ ያጸድቃል፡፡

26.3.6 የአክሲዮን ማህበሩ ዓላማዎች ግባቸውን እንዲመቱ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ይወስዳል

26.3.7 ከኢትዮጵያ ውጪ ስለሚከፈቱ ቅርንጫፎች ውሳኔ ይሰጣል፡፡

26.3.8 በዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚቀርቡለትን የኢንቨስትመንትና የቋሚ ንብረት ግዥ ጥያቄዎች ያጸድቃል፡፡

26.3.9 አስፈላጊ መስሎ የሚታየውን ማናቸውንም ምክረ ሃሳቦች ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

26.3.10 አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ተለይተው ለሚታወቁ ጉዳዮች ብቻ የዳይሬክተሮች ቦርድ ለቦርዱ ሰብሳቢ እና/ወይም ለዋና ሥራ አስፈፃሚ የውክልና ሥልጣን ሊሰጥ ይችላል፡፡

26.3.11 የዳይሬክተሮች ቦርድ ከላይ ከተጠቀሱት ስልጣኖች በተጨማሪ የማይንቀሳቀሱ ወይም የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን የመግዛት፣ የመሸጥ እና የመለወጥ ጉዳዮች ላይ መወሰን ሥልጣን አለው፡፡ ቦርዱ ይህን ሥልጣኑን በቃለ-ጉባዔ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

26.3.12 የዳይሬክተሮች ቦርድ የአክሲዮን ማሕበሩን የማይንቀሳቀሱ ቋሚ ንብረቶች በማስያዝ ለአክሲዮን ማሕበሩ ጥቅም መበደር ይችላል፡፡ ቦርዱ ይህን ሥልጣኑን በቃለ-ጉባዔ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

26.3.13 የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ብድሮችንና ሌሎች ተሰብሳቢ ክፍያዎችን መሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ መርሆችን በመከተል ከሂሳብ መዝገብ ላይ ሊሰርዝ ይችላል፡፡ እንዲሁም አገልግሎት መስጠት የማይችሉትን ቋሚ ንብረቶች ማስወገድ ወይም ከመዝገብ ለይ መሰረዝ ይችላል፡፡ ቦርዱ ይህን ሥልጣኑን በቃለ-ጉባዔ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

26.3.14 ቦርዱ የአክሲዮን ማሕበሩን የአክሲዮኖች ግዢ እና ሽያጭ አገልግሎቶች እና ሌሎች የገንዘብ ሠነዶችን በካፒታል ገበያ ላይ አገልግሎት መስጠትን እንዲሁም በካፒታል ገበያ ላይ ያሉ ሌሎች ተሳትፎዎችን ይወስናል፡፡

26.3.15 አንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በሕጉ፣ በመመሥረቻ ጽሑፍና በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ የተጣለበትን ኃላፊነት በሕጋዊ መንገድ በሚያከናውንበት ጊዜ ለሚከሰቱ ዕዳዎች በግል ተጠያቂ አይሆንም፡፡ ዳይሬክተሩ በቸልተኝነት፣ ወይም ኃላፊነቱን በማጉደል ለሠራው ሥራዎች ግን ከኃላፊነት ነጻ አይሆንም፡፡

## <u>አንቀጽ ሃያ ሰባት</u>

## <u>የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ የስብሰባ ቦታ፣ አጠራር እና የአሰራር ደንብ</u>

27.1 የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ እና ም/ሰብሳቢ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይመረጣሉ፡፡

27.2 ሰብሳቢው የቦርድ ስብሰባ የመጥራት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ በአክሲዮን ማሕበሩ ዋና ጽ/ቤት ወይም ሰብሳቢው በሚመርጠው በሌላ ቦታ ቢያንስ በወር 1/አንድ/ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡ ከዚህም ሌላ የአክሲዮን ማሕበሩ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በሚያስፈልገው መጠን ተጨማሪ ስብሰባዎች ሊያካሄድ ይችላል፡፡

27.3 የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው የቦርድ ስብሰባዎችን ሁሉ በሰብሳቢነት ያካሂዳል፡፡ ነገር ግን ሁለቱም በማይኖሩበት ጊዜ በስብሰባው በሚሰየም ማናቸውም የቦርድ አባል/ዳይሬክተር ይመራል፡፡

27.4 የዳይሬክተሮች ቦርድ የአክሲዮን ማሕበሩን መመሥረቻ ጽሑፍና የንግድ ሕጉን መሠረት በማድረግ የራሱን የአሠራር ሥነ-ሥርዓት ደንብ ማዘጋጀት ይችላል፡፡

## <u>አንቀጽ ሃያ ስምንት</u>

## <u>የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ</u>

28.1 ከጠቅላላው የዳይሬክተሮች ቁጥር 51% (ሃምሳ አንድ በመቶ) የሚሆኑት በስብሰባው ላይ በራሳቸው ወይም በወኪላቸው ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ካልተገኙ በስተቀር የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ማሳለፍ አይችልም፡፡ ውሳኔ የሚተላለፈው በድምጽ ብልጫ ነው፡፡ ማንኛውም ዳይሬክተር ወይም ተወካይ ድምጽ የመስጠት መብት ይኖረዋል፡፡ ድምጽ እኩል ለእኩል በሚከፈልበት ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ የደገፈው ሀሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

28.2 በቦርድ ስብሰባ ለመገኘት የማይችል ዳይሬክተር የሚወከለው በሌላ ዳይሬክተር ብቻ ይሆናል፡፡ አንድ ዳይሬክተር ሊወክል የሚችለው አንድ ሌላ ዳይሬክተር ብቻ ነው፡፡

28.3 የቦርድ ውሳኔዎች በቃለ-ጉባዔ ተይዘው በስብሰባው ላይ በተገኙ ዳይሬክተሮች እና በማህበሩ ጸሐፊ ይፈረማሉ፡፡ ቃለ-ጉባዔዎች በመዝገብ ይቀመጣሉ፡፡

28.4 የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባን በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለማድረግ ይቻላል፡፡

28.5 የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎችን በሚሰጥበት ጊዜ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ባለሞያዎችን ሊያማክር ይችላል፡፡

28.6 የውሳኔ ቅጂዎች በሰብሳቢው እና በማህበሩ ጸሐፊ እየተረጋገጡ መፈረም አለባቸው፡፡

## <u>አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ</u>

## <u>ዳይሬክተሮችን ስለመተካት</u>

29.1 የዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 23.1 ድንጋጌ ቢኖርም፣ በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ዳይሬክተሮች በአንቀጽ 29.3 ላይ በተመለከቱት እና በማናቸውም ምክንያቶች ከቦርድ አባልነት የለቀቁ ወይም የተገለሉ እንደሆነ ያሉት ዳይሬክተሮች ለቀሪው የሹመት ጊዜ የሚተኩ ሌሎች ዳይሬክተሮችን አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት መሰየም ይችላሉ፡፡

29.2 የቦርድ አባላት በማናቸውም ጊዜ ቁጥራቸው ከ50% በታች የቀነሰ እንደሆነ የቀሩት አባላት የጐደሉትን ለማሸም አባላቱ ከጐደሉበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ጠቅላላ ጉባዔውን መጥራት አለባቸው፤ በጐደሉት አባላት ምትክ ሹመት እስኪደረግ ድረስ የቀሩት አባላት አክሲዮን ማሕበሩን ያስተዳድራሉ፡፡

29.3 በሚከተሉት ምክንያቶች አንድ ዳይሬክተር ከቦርድ አባልነቱ ሊገለል ይችላል፡-

29.3.1 ዳይሬክተሩ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ሲከስር ወይም ዕዳውን መክፈል ሲሳነው ወይም በዕዳው ምክንያት ሲዋሀድ፣

29.3.2 የአዕምሮ ቀውስ ሲደርስበት፣

29.3.3 በወንጀል ተከሶ ሲፈረድበት፣

29.3.4 ዳይሬክተሩ እያወቀ ከአክሲዮን ማሕበሩ ጋር የጥቅም ግጭት የሚፈጥሩ ተግባራቶች ላይ ሲሰማራ፣

29.3.5 ዳይሬክተሩ የአክሲዮን ማሕበሩን ጥቅም ለማስጠበቅ እርምጃ መውሰድ ሲሳነው፣

29.3.6 ቦርዱ በስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ እና በሥነ-ምግባር ደንብ ውስጥ በደነገገው ሌላ ምክንያት፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ

## አክሲዮኖችን በዋስትና ስለማስቀመጥ

30.1. ዳይሬክተሮች ኃላፊነታቸውንና ተግባራቸውን በትክክልና በሚገባ ለመወጣታቸው ዋስትና ይሆን ዘንድ እያንዳንዳቸው 25 /ሃያ አምስት/ የተመዘገቡ አክሲዮኖች በአክሲዮን ማሕበሩ ዘንድ ማስያዝ አለባቸው፡፡

30.2. ዳይሬክተሮቹ ዳይሬክተርነታቸውን ካልለቀቁና አክሲዮን ማሕበሩ በኃላፊነታቸው የሚፈለግባቸው ምንም ነገር አለመኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር ዋስትናቸው አይወርድም፡፡

30.3. አክሲዮን ማሕበሩ ለቦርድ አባላቶቹ የሙያ ዋስትና ኢንሹራንስ ሊገባላቸው ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ አንድ

## የዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ምክትል ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎች፣ የውስጥ ኦዲት ኃላፊ እና የሪስክ እና ኮምፕሊያንስ ኃላፊ

31.1. የአክሲዮን ማሕበሩ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይሾማል፡፡

31.2. በዋና ሥራ አስፈፃሚው አቅራቢነት ቦርዱ ምክትል ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎች፣ የውስጥ ኦዲት ኃላፊ እና የሪስክ እና ኮምፕሊያንስ ኃላፊ ይሾማል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ሁለት

## የዋና ሥራ አስፈፃሚ ሥልጣንና ተግባር

32.1. አክሲዮን ማህበሩ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ይኖረዋል፡፡

32.2. የዋና ሥራ አስፈፃሚው ተጠሪነት ለቦርድ ሆኖ፤ ደመወዙና ጥቅማጥቅሙም በቦርዱ ይወሰናል፡፡

32.3. የአክሲዮን ማህበሩን ጠቅላላ የዕለት ተዕለት ሥራ ይመራል፤ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት አክሲዮን ማህበሩን ይወክላል፡፡ የአክሲዮን ማሕበሩን ዋና ሥራ አስፈፃሚና ከፍተኛ ተጠሪ በመሆን የአክሲዮን ማሕበሩን አስተዳደር በበላይነት ለመምራት አጠቃላይ ሥልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

32.4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

32.4.1. በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማሟላት በአክሲዮን ማሕበሩ ስም እና አክሲዮን ማሕበሩን ወክሎ ይሠራል፤

32.4.2. አክሲዮን ማሕበሩ በዓለም አቀፍ እና በሀገር ውስጥ በሚያካሄዳቸው ሥራዎች ምክንያት በሦስተኛ ወገኖች፣ በመንግሥታትና የግል ድርጅቶች በአክሲዮን ማሕበሩና በሌሎች የገንዘብ ተቋማት ዘንድ ይወክላል፤

32.4.3. የአክሲዮን ማህበሩን የሥራ ዕቅድና በጀት፤ የረዥም ጊዜ ስትራቴጂና ፖሊሲዎች አዘጋጅቶ ለቦርድ ማቅረብ፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

32.4.4. የሥራ መመሪያ፤ ፕሮሲጀር፣ ጋይድላይን እና ሌሎች የአሰራር ሥነ-ሥርዓቶችን መቆጣጠሪያ ሠነዶች ያዘጋጃል፤ ያጸድቃል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

32.4.5. የሥራ ድርሻን ኃላፊነት፤ ሥልጣን የሥራ ክፍፍል የሚያሳይ የአክሲዮን ማህበሩን ድርጅታዊ መዋቅር /የኦርጋናይዜሽንናል ስትራክቸር/ አዘጋጅቶ ለቦርድ ማቅረብ፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

32.4.6. የዋና ሥራ አስፈፃሚ ምክትል የሆኑ ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎች /ሲነየር ኤክስኪዮቲቭ ኦፊሰሮች/ ይመርጣል፤ ለቦርድ በማቅረብ ሹመታቸውን ያጸድቃል፤

32.4.7. የአክሲዮን ማሕበሩን የሂሳብ አያያዝ በሚመለከት አመራር ይሰጣል፤ ተገቢውን ቁጥጥር ያደርጋል፤

32.4.8. የአክሲዮን ማሕበሩን የዕለት ተዕለት ሥራ ለማከናወን መደበኛ የማኔጅመንት ስብሰባዎችን ያደርጋል፤

32.4.9. በሕጉ፣ በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍና በባለአክሲዮኖች ጉባዔ በሚወሰነው መሠረት የተፈቀደለትን የመጠባበቂያ ሂሳብ እና ሌሎች የመጠባበቂያ ሂሳቦችን ያቋቁማል፤

32.4.10. በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍና በዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ መሠረት የተሰጡትን ሥልጣኖች ለአክሲዮን ማሕበሩ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

32.4.11. የአክሲዮን ማሕበሩን ጥቅም ለመጠበቅ ለማሕበሩ ነገረፈጅ ለመቅጠር/ለመወከል፣ ጠበቃ ለማቆም/ለመወከል፣ ሌሎች ወኪሎች ለመሾም እንዲሁም ሌሎች ባለሞያዎች ለመቅጠርና ለማሰናበት ሥልጣን ይኖረዋል፤

32.4.12. የባንክ ሒሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፣ ይዘጋል፤

32.4.13. የሃዋላ፣ ቼኮችን፣ የምንዛሪ ሠነዶችን፣ የተስፋ ሠነዶችን ሌሎች የማይተላለፉ ሠነዶችን እንዲሁም የገቢና ወጪ ንግድ ማስታወቂያዎችን ይፈርማል፣ ያጸድቃል፣ ቅናሽ ያደርጋል፤

32.4.14. አክሲዮን ማሕበሩን ከኪሳራ፤ ከጥፋት፣ ከድንገተኛ አደጋና ከማናቸውም ዓይነት ዕዳ ለመጠበቅ የሚያስችል የመድን ዋስትና ከታወቀ የመድን ኩባንያ ወይም ሰው ጋር ይዋዋላል፤

32.4.15. በዳይሬክተሮች ቦርድ ቅድሚያ ፍቃድ መሠረት ከአክሲዮን ማሕበሩ ዓላማዎች ሳይወጣ በሥራ ላይ ያልዋለውን ገንዘብ ኢንቨስት ያደርጋል ወይም በአትራፊ ሥራ ላይ ያውላል፤

32.4.16. ዋና ሥራ አስፈፃሚው በቦርድ ከሚሰየሙት ኃላፊዎች በስተቀር በሕግ አግባብ ሠራተኛ የመቅጠር፣ የማሳደግ፣ ከደረጃ ዝቅ የማድረግና የማሰናበት ሥልጣን አለው፤

32.4.17. የአክሲዮን ማሕበሩን የሥራ ዕቅድ እና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርድ በማቅረብ ያጸድቃል፤

32.4.18. የአክሲዮን ማሕበሩን ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ የሚመለከት ዘገባ ያቀርባል፤

32.4.19. በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ውስጥ መደረግ ስለሚያስፈልጋቸው ማናቸውም ማሻሻያዎች ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሃሳብ ያቀርባል፤

32.4.20. ለአክሲዮን ማሕበሩ የዕለት ከዕለት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ሕጋዊ ወጪዎችና ክፍያችን ይፈቅዳል፤

32.4.21. በቦርዱ ሰብሳቢ ሲጠየቅ ከማህበሩ ጸሐፊ ጋር በመተባበር የቦርዱን ረቂቅ የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፤

32.4.22. ከቦርዱ ሰብሳቢ ጋር በመመካከር እና ከማህበሩ ጸሐፊ ጋር በመተጋገዝ የቦርድ ስብሰባዎችን ዝግጅት ያስተባብራል፣

32.5. በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ያልተጠቀሱ ነገር ግን ለአክሲዮን ማህበሩ ዓላማዎች መሳካት አስፈላጊ የሆኑትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

32.6. በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሰጡትን ተግባራት የማከናወንና የቦርዱን ውሳኔዎች የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ሦስት

## የውጭ ኦዲተር ስያሜ፤ ኃላፊነትና ተግባር

33.1. የአክሲዮን ማሕበሩ የውጭ ኦዲተር በባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይሰየማል፡፡

33.2. የአክሲዮን ማሕበሩ የውጭ ኦዲተር ተግባርና ኃላፊነት በንግድ ሕግ፤ በመድን ሥራ አዋጅ፤ በኢትጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት ይፈፀማል፡፡

33.3. የውጭ ኦዲተር ስለሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ፣ ስለንብረት እና ዕዳ ተመን፣ መሠረታዊ የሂሳብ መርሆዎች እና አግባብነት ባላቸው ሕጐች መሠረት ኃላፊነቱን በጥንቃቄ ማከናወን አለበት፡፡

33.4. የውጭ ኦዲተር ሪፖርት ከአክሲዮን ማሕበሩ የበጀት ዓመት ማብቂያ በኃላ አግባብነት ባላቸው ሕጐች ላይ በተደነገገው መሠረት ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ይሰጣል፡፡

33.5. የውጭ ኦዲተሮች የሦስት ተከታታይ ሂሳብ ዓመት ኦዲት እንዲያደርጉ በጠቅላላ ሊሾሙ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ አራት

## የማህበሩ ጸሐፊ ሹመት፤ ሥልጣንና ተግባር

34.1. የማህበሩ ጸሐፊ በዋና ሥራ አስፈፃሚው አቅራቢነት በዳይሬክተሮች ቦርድ ይሾማል፡፡ የማህበሩ ጸሐፊ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

34.1.1 የአክሲዮን ማሕበሩን መረጃዎችና መዛግብት የማደራጀትና የመያዝ፤

34.1.2 ለሚመለከተው አካል ሪፖርቶችንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በወቅቱ የመስጠት፤

34.1.3 ለባለአክሱዮኖችና ለሦስተኛ ወገኞች መረጃ የመስጠት፤

34.1.4 የባለአክሲዮኖችና የቦርድ አባላትን ስብሰባዎች የማዘጋጀት፤

34.1.5 ቃለ-ጉባኤዎችን ማዘጋጀትና አደራጅቶ የመያዝ፤ እና

34.1.6 በዋና ሥራ አስፈፃሚው እና በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን፡፡

## ምዕራፍ አራት

## ስለአክሲዮን ማሕበሩ ሂሳብ አያያዝና ተዛማጅ ተግባራት

### አንቀጽ ሰላሳ አምስት

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አግባብነት ባላቸው ሕጎች እና በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ውስጥ ስለሂሳብና መዝገብ አያያዝ የተደነገጉት ለአክሲዮን ማሕበሩ ሂሳብ አያያዝና አመዘጋገብ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

### አንቀጽ ሰላሳ ስድስት

### የፋይናንስ መዝገቦችና መረጃዎች

36.1 አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የአክሲዮን ማሕበሩን የሥራ እንቅስቃሴ እና ያለውን የገንዘብ አቋም በግልጽና በትክክል የሚያስረዳ መዝገቦች በአግባቡ መያዝ አለበት፡፡

36.2 አክሲዮን ማሕበሩ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት ዝርዝር ጉዳዩን ወዲያውኑ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ አለበት፡፡

36.3 ለመድን ገቢዎች ወይም ለሌሎች መድን ሰጪዎች/አበዳሪዎች ግዴታውን ለመፈፀም ለመወጣት ያልቻለ ከሆነ፣

36.4 ለመድን ገቢዎች ወይም ሌሎች መድን ሰጪዎች/ አበዳሪዎች የሚያደርገውን ክፍያ ለማቋረጥ የተገገደ ሲሆን፣

### አንቀጽ ሰላሳ ሰባት

### የማህበሩ የሂሳብ ዓመትና ሪፖርት

37.1 የአክሲዮን ማህበሩ የሂሳብ ዓመት እ.ኤ.አ ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ በሚቀጥለው ዘመን ሰኔ 30 ያበቃል፡፡

37.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ በእያንዳንዱ የሂሳብ ዘመን ማብቂያ ላይ ቦርዱ በዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚቀርብለትን ሪፖርት መነሻ በማድረግ የአክሲዮን ማህበሩን አጠቃላይ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፡፡

37.3 ሪፖርቱ ስለአክሲዮን ማህበሩ ትርፍና ኪሳራ እንዲሁም ስለዳይሬክተሮችና ስለኦዲተሮች ክፍያ ዝርዝር መረጃና እንዲሁም ስለመጠባበቂያ ገንዘብ ምደባና ስለዘመኑ የትርፍ ድርሻ አመዳደብ ሃሳቦችን ያቀፈ ሆኖ መገኘት አለበት፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ስምንት

## የሂሳብ ሠነዶችን እና ሪፖርቶችን ስለመስጠት

በንግድ ሕጉ አንቀጽ 427 መሠረት የአክሲዮን ማሕበሩ የንብረት ዝርዝር (Inventory)፣ የሀብት እና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ፣ የትርፍና የኪሳራ መግለጫ እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት የዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ከመደረጉ ቢያንስ ከ40 (አርባ) ቀናት አሰቀድሞ ለኦዲተሮች እና ለሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መላክ አለበት፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ

## በጥሬ ገንዘብ ስለሚያዙ ሂሳቦችና የመጠባበቂያ ገንዘብ

39.1 አክሲዮን ማሕበሩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የመቶኛ ስሌት መጠን ጥሬ ገንዘብ እና ጥሬ-ገንዘብ አካል የሆኑ ሠነዶችን /ሊኩይድ አሴት/ ይይዛል፡፡

## አንቀጽ አርባ

## በቸልተኝነት ወይም እምነት ማጉደል ምክንያት ለሚደርሱ ኪሣራዎች የሚሸፈኑባቸው መጠባበቂያዎች

40.1 አክሲዮን ማሕበሩ በማናቸውም የወንጀል ድርጊት፣ ቸልተኝነት ወይም እምነት ማጉደል ምክንያት በአክሲዮን ማሕበሩ ላይ ለሚደርስ ኪሣራ መሸፈኛ የሚሆን መጠባበቂያ ገንዘብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስተያየት ይበቃል ተብሎ የሚታመንበትን መጠን ሂሳብ ሊይዝ ይችላል፡፡

40.2 ከእንደዚህ ዓይነቱ ኪሣራ ራሱን ለመጠበቅ አክሲዮን ማሕበሩ ተገቢ ፈቃድ ካለው ዕውቅ የመድን ድርጅት ዘንድ የመድን ዋስትና ሊገባ ይችላል፡፡

## አንቀጽ አርባ አንድ

## ሌሎች የመጠባበቂያ ሂሳቦች

41.1 አክሲዮን ማሕበሩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ የሚጠይቀውን በማሟላት ቀጥሎ የተመለከቱትን ወጭዎች የሚሸፍኑ የመጠባበቂያ ሂሳቦች ሊይዝ ይችላል፡፡

41.1.1 የንብረት እርጅና ቅናሽ እና የተጠራቀመ የእርጅና ቅናሽ፣

41.1.2 በየዓመቱ ለተጠራቀሙ ኪሳራዎች መሸፈኛ፣

41.1.3 በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ተፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች ወጭ የሚሆን ሌላ መጠባበቂያ ሂሳብ መያዝ አለበት፡፡

## አንቀጽ አርባ ሁለት

## የትርፍ ድርሻ አመዳደብና አከፋፈል

42.1 በንግድ ሕጉ ከአንቀጽ 432 እስከ አንቀጽ 439 የተደነገጉት እና በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 39 ላይ የተቀመጠው እንደተጠበቁ ሆኖ የትርፍ ክፍፍሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚያቀርበው ሃሳብ መሠረት፣ የአክሲዮን ማሕበሩ ኦዲተሮች ከመረመሩትና የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ካጸደቀው በኂላ ከተጣራ ትርፍ ላይ ታክስ፣ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ፣ በባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የተፈቀዱ ሌሎች የመጠባበቂያ ገንዘቦች፣ ያለፉት ኪሳራዎች እና ሌሎች ተቀናሾች ከተቀነሱ በኃላ በአንድ ጊዜ ክፍያ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

42.2 ትርፍ ለባለአክሲዮኖች በሚከፋፈልበት ጊዜ የሚከተሉት ሁለት ነገሮች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡-

42.2.1 ከተከፈለው ጠቅላላ ካፒታል ውስጥ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ያለው የተከፈለ ካፒታል መጠን፣

42.2.2 በበጀት ዓመቱ ውስጥ የአክሲዮኖች ዋጋ በሙሉ ወይም በከፊል ተከፍሎ በአክሲዮን ማሕበሩ እጅ የቆየበት ጊዜ ናቸው፡፡

42.3 የትርፍ ድርሻ የሚከፈልበት ቀንና ሁኔታ በባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ አርባ ሦስት

## ካፒታል በሚቀነስበት ጊዜ የሚደረግ የትርፍ ክፍፍል ዕገዳ

የአክሲዮን ማሕበሩ ዋና ካፒታልና መጠባበቂያ ሂሳብ ከሚገባው በታች በሚቀንስበት ጊዜ ጉድለቱን ለማስወገድ የሚቻልበተ እርምጃ በብሔራዊ ባንክ ውሳኔ መሠረት ከሚደረገው የገንዘብ ማዘዋወር በስተቀር፣ በዋናው ካፒታል ላይ የታየው ቅናሽ በሕጉ መሠረት ሙሉ በሙሉ እስኪተካ ድረስ አክሲዮን ማሕበሩ በማናቸውም ጊዜ ትርፉን አያሳውቅም ወይም አያከፋፍልም ወይም ከትርፍ ላይ ምንም ዓይነት የገንዘብ ዝውውር አይፈፅምም፡፡

## አንቀጽ አርባ አራት

## ስለምዝገባና ሪፖርቶችን ይፋ ስለማድረግ

44.1 በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ የሚደረገው ማናቸውም ማሻሻያ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ከጸደቀ በኋላ አግባብ ባለው ሕግ በተደነገገው መሠረት ይመዘገባል፡፡

44.2 አክሲዮን ማህበሩ በውጭ ኦዲተሮች የተረጋገጠ የሂሳብ ሚዛን፤ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሰራጭ ጋዜጣ እንዲታተም ይደረጋል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## ስለአክሲዮን ማሕበሩ መፍረስ እና ሂሳብ ስለማጣራት

## አንቀጽ አርባ አምስት

## የአክሲዮን ማህበሩን ለማፍረስ የሚያበቁ ምክንያቶች እና አግባብነት ያላቸው ሥነ-ሥርዓቶች

45.1 የአክሲዮን ማህበሩ አግባብ ባለው ሕግ በተመለከተውና በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሠረት ሊፈርስ ይችላል፡፡

45.2 ከሚከተሉት ምክንያቶች ውስጥ ማናቸውም ቢሆን ለአክሲዮን ማህበሩ መፍረስ ሂሳብ ማጣራት በቂ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

45.2.1 የማህበሩ ዓላማ ተግባራዊ ሳይሆን ሲቀር ወይም ማህበሩ ተግባሩን ለማከናወን ከአቅሙ በላይ የሆኑ ምክንያቶች ሲያጋጥሙት፤

45.2.2 አክሲዮን ማህበሩ በፈቃደኝነት እንዲፈርስ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሲወሰን፤

45.2.3 ማናቸውም የጥቅም መብት ያለው በሚያቀርበው አቤቱታ መሠረት ፍ/ቤት አክሲዮን ማህበሩ የሚፈርስበት በቂ ምክንያት መኖሩን በማረጋገጥ እንዲፈርስ ትዕዛዝ ሲሰጥ፤

45.2.4 አክሲዮን ማህበሩ በመክሰሩ ምክንያት የዕዳ ማጣራትና የኪሳራ ፋይል በፍ/ቤት ሲከፈት፤

45.2.5 ካፒታሉ በሦስት አራተኛ ሲቀንስ፤

45.3 አክሲዮን ማህበሩ እንዲፈርስ ጠቅላላ ጉባዔው ሲወስን ሂሳብ አጣሪዎችን ይሾማል።

45.4 ማንኛውም የአክሲዮን ማህበሩ አባልም ሆነ ኦዲተር የሂሳብ አጣሪዎችን ሹመት በመቃወም ያመለከተ እንደሆነ የቀረበው መቃወሚያ በቂ ምክንያት ያለው ሆኖ ካገኙት ጠቅላላ ጉባዔው ሹመቱን ሊሽረው ወይም ሊያስቀረው ይችላል።

## ምዕራፍ ስድስት

## ሌሎች ድንጋጌዎች

### አንቀጽ አርባ ስድስት

### አክሲዮን ማህበሩ በሥራ የሚቆይበት ጊዜ

አክሲዮን ማህበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው።

### አንቀጽ አርባ ሰባት

### ልዩ ልዩ ጉዳዮች

47.1. ይህ የመመሥረቻ ጽሑፍ፤ በማናቸውም ጊዜ በባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሊሻሻል ይችላል።

47.2. በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍና አግባብነት ባላቸው አስገዳጅ ሕጎች መካከል መቃረን ሲኖር አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈጻሚ ይሆናሉ። በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ውስጥ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ በንግድ ሕጉና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉትን በመከተል ይተገበራል።

47.3. በዚህ የመመሥረቻ ጸሑፍ የአማርኛው ቅጂና የእንግሊዘኛው ቅጂ መካከል የትርጉም ልዩነት የተፈጠረ እንደሆነ የአማርኛው ቅጂ ተፈፃሚ ይሆናል።

ይህ መመሥረቻ ጽሑፍ በባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ከጸደቀ በኋላ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ሲያገኝ እና በሚመለከተው አካል ሲመዘገብ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ መስከረም ----- ቀን 2017 ዓ.ም

--------------------------------